| የተበደለ(ች) እና ትኩረት የተነፈገው(ች) ልጅ ማጤን እና ሪፖርት ማድረግ |
|---|
| የኮቪድ -19 ማረጋገጫ |
| ከበጎ ፈቃደኞች በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች FY22 |

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪዎቻችንን ጥረቶች ለማገዝና ለማበልፀግ በት/ቤቶቻችን ለሚሰሩ በጎ-ፈቃደኞች ከፍ ያለ አክብሮት አለው። እንደማህበረሰብ፤ ለተማሪዎቻችን ሰላማዊ፣ እንክብካቤ የሚያገኙባቸው አካባቢዎችን መፍጠር የጋራ ሀላፊነታችን መሆኑን እንገነዘባለን። እነዚህ አዘውትረው ለሚቀርቡ ጥያቄዎች (FAQs) የተዘጋጁት መልሶች ለበጎ-ፈቃደኛ ስልጠና እና ዳራ የማጣራት ተግባር ያገለግላሉ።

ይህ በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች ሰነድ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ JHC የሕፃናት በደል እና ቸልተኝነት፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ JHC-RA፣ የሕፃናት በደል እና ችላ ማለትን ሪፖርት ማድረግ እና መመርመር፣ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ IRB-RA፣ በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያገለግሉ በጎ ፈቃደኞች ደንቦች ጋር የሚጣጣም እና የተደገፈ ነው። ስለ ልጅ መበደል እና በቸልተኝነት መተው እዚህ ድረ-ገጽ ላይ ተጨማሪ መረጃ ይገኛል:- https://www.montgomeryschoolsmd.org/childabuseandneglect/

### *የጎብኚ(ዎች) ማኔጅመንት ስርዓት:-*

| *ጥያቄ* | *መልስ* |
|---|---|
| **ጥ 1:- ጎብኚዎች፣ በጎፈቃደኞችን ጨምሮ ትምህርት ቤት በሚደርሱበት ወቅት ምን ማድረግ አለባቸው?** | **መ 1:-** በተመደበው የትምህርት ሰዓት ጎብኚዎችና በጎ ፈቃደኞች ጭምር ሁሉም (VMS) በመጠቀም ወደ ትምህርት ቤቶች ለመግባት መመዝገብ አለባቸው። |
| **ጥ 2:- የጎብኚዎች ማኔጅመንት ሲስተም "Visitor Management System (VMS)" ምንድነው?** | **መ 2:-** VMS የጎብኚዎችን የመንጃ ፈቃድ ወይም ከስቴት የተሰጠ መታወቂያ ካርድ በስቴቱ የጾታዊ ጥቃት ወንጀለኝነት መዝገብ ላይ ይቃኛል። VMS በትምህርት ቤት ሕንፃ ውስጥ ሁል ጊዜ ሊለበስ የሚገባውን የስም መለያ ያወጣል። |

### *የበጎ-ፈቃደኛ ስልጠና አስፈላጊነት:-*

| *ጥያቄ* | *መልስ* |
|---|---|
| **ጥያቄ 3 - በጎ ፈቃደኞች ሥልጠና ያስፈልጋቸዋል? ለበጎ ፈቃደኞች እና ለኮንትራክተሮች የሕፃናት በደል እና ቸልተኝነትን ስለማወቅ እና ሪፖርት ማድረግ** | **መ 3:-** አዎ። ትምህርት ቤቶችን እና ተማሪዎችን **በመደበኛነት** የሚደግፉ እና በመስክ ጉዞዎች የሚሳተፉ በጎ ፈቃደኞች ሁሉም የበይነመረብ ሞጁሉን ማጠናቀቅ አለባቸው፣ የሕፃናት በደል እና ችላ ማለትን ማወቅ እና ሪፖርት ማድረግ ለበጎ ፈቃደኞች እና ለኮንትራክተሮች ሥልጠና። ይህ የስልጠና አስፈላጊነት በትምህርት ቤት የሚደገፉ እንቅስቃሴዎችን በመደበኛነት በበጎ ፈቃደኝነት በሚረዱ ሁሉ ላይ ይሠራል። |
| **ጥ 4:- እኔ ይህንን ስልጠና እንዴት ማግኘት እችላለሁ?** | **መ 4:** ሥልጠናው በልጆች ላይ በደል እና ቸልተኝነት ድረ -ገጽ ላይ [እዚህ ](#)ይገኛል። |
| **ጥ 5:- ማንኛውም ለትምህርት ቤት ድጋፍ የሚሰጥ/የምትሰጥ ሰው የስልጠና መስፈርቶቹን ማጠናቀቅ አለበ(ባ)ት?** | **መ 5 :-** ሁሉም የማህበረሰብ አባላት በዚህ መረጃ ሰጭና አስፈላጊ የሆነ ሥልጠና ላይ እንዲሳተፉ የምናበረታታ ሲሆን፤ በአሁኑ ጊዜ ግን **አዘውትረው** ትምህርት ቤቶችን የሚደግፉ ግለሰቦችን ብቻ ስለ ሕፃናት በደል እና ቸልተኝነት ስልጠና እንዲያጠናቅቁ እንፈልጋለን። ነገር ግን፣ ይህ ግዴታ በት/ቤት ሰራተኞች ቁጥጥር በትላልቅ ዝግጅቶች ላይ ድጋፍ የሚያደርጉ ወይም ለአንድ ወቅት በዝግጅት የሚያግዙ ግለሰቦች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም። የበጎ ፈቃደኝነት ሥልጠና ማጠናቀቅ (አጠቃላይ ዝርዝር ሳይሆን) **የማያስፈልጋቸው** የእንቅስቃሴ ዓይነት ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው።<br>• የ MCPS ሰራተኛ የሚቆጣጠራቸው በመማርያ ክፍሎች እንግዳ አንባቢዎችና ተናጋሪዎች፤<br>• ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/ኮሌጅ መልማዮችና በጎፈቃደኞች በምልመላ ስራ ላይ ሲሆኑ እና በኮሌጅ አውደርዕይ ጊዜ፣<br>• ክብረ በዓሉ ላይ የተገኙ ወይም በመርዳት ላይ የሚገኙ (ለምሳሌ:- የሠልፍ ትርኢት) ወይም ክፍል ውስጥ በተዘጋጀ ፓርቲ የሚረዱ ወላጅ/ሞግዚቶች ወይም ሌሎች ዘመዶች፣ እና<br>• በትልልቅ ሁነቶች-ዝግጅት የቲኬት መሸጫ ልዩ ዋጋ እና መደብሮች ላይ የሚሠሩ ወላጆች/ሞግዚቶች. |
| **ጥ 6:- የበጎፈቃደኛ ስልጠና የሚገኘው መቼ ነው?** | **መ 6:** ሥልጠናው በልጆች ላይ በደል እና ቸልተኝነት ድረ -ገጽ ላይ [እዚህ ](#)ይገኛል። |
| **ጥያቄ 7-በ 2019-2020 ወይም 2020-2021 የትምህርት ዓመት ውስጥ የ MCPS ሥልጠናን ቀደም ብዬ ከጨረስኩ፣ በ 2021-2022 የትምህርት ዓመት እንደገና መውሰድ አለብኝ?** | **መ 7:-** የ MCPS ሪኮርዶች አንድ ግለሰብ ባለፈው ዓመት የ MCPS ሥልጠናውን እንደጨረሰ የሚያንፀባርቁ ከሆነ ግለሰቡ(ቧ) በ 2021-2022 የትምህርት ዓመት ተጨማሪ ሥልጠና መውሰድ አያስፈልገውም ወይም አያስፈልጋትም። ስልጠናው መወሰድ ያለበት በየሦስት ዓመቱ ነው። የበጎ-ፈቃደኛ ስልጠና ተወስዶ ከሆነ:-<br>• 2018-2019 በ 2021-2022 መታደስ አለበት<br>• 2019-2020 በ 2022-2023 መታደስ ይኖርበታል<br>• 2020-2021 በ 2023-2024 ይታደሳል |
| **ጥ 8:- በጎፈቃደኞች በሙሉ የስልጠና ሞዱሉን በድረ-ገጽ ማጠናቀቅ አለባቸው?** | **መ 8:** ሁሉም በጎ ፈቃደኞች የኤሌክትሮኒክስ ማረጋገጫ ለማግኘት ስለ ልጆች በደል እና ቸልተኝነት ድረ -ገጽ ላይ ኦንላይን ሥልጠናውን ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል እዚህ ይህ መስፈርት መጠናቀቁን ለማረጋገጥ።<br><br>አንድ በጎ ፈቃደኛ **የሕፃናት በደል እና ቸልተኝነት ሥልጠናውን ቀድሞውኑ ካጠናቀቀ(ች)**፣ በጎ ፈቃደኛው(ዋ)/ሥራ ተቋራጩ ማጠናቀቁ(ቋ)ን የሚገልጽ ሪፖርት በ myMCPS (ደንበኛ ማክበር ስር) ስሙ(ሟ) ይታያል። |

| | |
|---|---|
| | <br><br>አንድ በጎ ፈቃደኛ **የሕፃናት በደል እና ቸልተኝነት ሥልጠናውን ካላጠናቀቀ(ች)**፣ ይህንን ለማድረግ አካውንት ያስፈልጋቸዋል። ወላጆች ወይም ሞግዚቶች የ MCPS Parent Portal አካውንት መጠቀም ወይም መክፈት ይችላሉ፣ ነገር ግን ወላጆች ያልሆኑት በዚህ [link](link) አካውንት ለመፍጠር ይችላሉ።[ሪሶርስ/resource](resource) ወላጆች/ሞግዚቶች የ MCPS Parent Portal አካውንት ቢከፍቱ ትምህርት ቤቶችን ይረዳል። አንዴ አካውንታቸውን ካገኙ በኋላ፣ ስልጠናውን ለማጠናቀቅ እና ስለማጠናቀቃቸውም በኮርስ ስልጠና ላይ ሪኮርድ ሊኖራቸው ይችላል። በኮርስ ውጤት 100% ከተመዘገበ የሕፃናት በደል እና ቸልተኝነት ስልጠና መጠናቀቁን ማረጋገጫ ይሆናል። ትምህርት ቤቶች ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው ሊንክ ሪፖርቱን ለማግኘት ይችላሉ፣ ነገር ግን በጎ ፈቃደኞች ውጤታቸውን ለትምህርት ቤት ማቅረብ ካለባቸው በፈለጉበት ጊዜ ሁሉ ወደ ኮርስ ስልጠና አካውንት ተመልሰው ሊያገኙት ይችላሉ። በዚህ የሪፖርት ማቅረቢያ ቅርጸት ምክንያት ትምህርት ቤቶች **ለበጎ ፈቃደኞች ወይም ለአነስተኛ ቡድን የሥልጠና ክፍለ ጊዜዎችን ለመስጠት ኦንላይን ሞጁሉን እንደ መገልገያ የመጠቀም አማራጭ** አይኖራቸውም።<br>አኮሞዴሽን የሚያስፈልጋቸው ወላጆች/አሳዳጊዎች በትምህርት ቤቶች ከመሳተፍ አይታገዱም። ለአኮሞዴሽን ጥያቄዎች የተማሪ አመራር እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች (SLEA)፣በ 240-740-3977 ያነጋግሩ። |
| **ጥ9፡- የአካል ስንክልና ላለባቸው ስልጠና ለመሙላት "accommodations" የሚያስፈልገኝ ከሆነስ ምን ይደረጋል?** | **መ 9 ፦** ርእሰ መምህራን እና የትምህርት ቤት ሰራተኞች እንደአስፈላጊነቱ ከ SLEA ጋር በመመካከር በት/ቤቶቻቸው ውስጥ ያሉ ግለሰቦችን እንደ አግባብነቱ ማስተናገድ አለባቸው። [መ 8 ይመልከቱ] |
| **ጥ10፡- የድረ-ገጽ የበጎፈቃደኛ ስልጠና በተለያዩ ቋንቋዎች ይሰጣል?** | **መ** 10 ፦ አዎ። በአሁኑ ጊዜ ኦንላይን ሥልጠና በ **እንግሊዝኛ፣ ስፓኒሽ፣ ቻይንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ኮሪያኛ፣ አማርኛ፣ ቬትናምኛ፣ እና በ ፖርቹጋልኛ** ይገኛል። |
| **ጥ11፡- በጎፈቃደኞች ስልጠና ማሟላታቸውን እንዴት እናውቃለን?** | **መ** 11፡- በጎ ፈቃደኞች ሥልጠናውን ሲያጠናቅቁ በስልጠናው መሳተፋቸው ሪኮርድ ስለሚደረግ በ MCPS ይመዘገባል። አዲሱ አሠራር በ MCPS Parent Portal አካውንት ያስፈልጋል፣ ስለማጠናቀቃቸው ማረጋገጫ በ100% የኮርስ ውጤታቸው ላይ ይመዘገባል። ትምህርት ቤቶች ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው ሊንክ ሪፖርቱን ለማግኘት ይችላሉ፣ ነገር ግን በጎ ፈቃደኞች ውጤታቸውን ለትምህርት ቤት ማቅረብ ካለባቸው በፈለጉበት ጊዜ ሁሉ ወደ ኮርስ ስልጠና አካውንት ተመልሰው ሊያገኙት ይችላሉ። |
| **ጥ12፡- በጎፈቃደኞች ስልጠናውን ከወሰዱ፣ ከተማሪዎች ጋር ይሠራሉ?** | **መ** 12፡- አዎ። ት/ቤት ባዘጋጃቸው የተለያዩ መንገዶች በጎፈቃደኞች ትምህርት ቤትን ለመርዳት ይችላሉ። |
| **ጥ13፡- ከልጆቻቸው ጋር ምሣ የሚመገቡ ወላጆች/ሞግዚቶች የድረ-ገጽ ስልጠና መሙላት ይጠበቅባቸዋል?** | **መ** 13፡- አይደለም ካፍቴሪያ ውስጥ ከልጆቻቸው ጋር ምሣ የሚመገቡ ወላጆች/ሞግዚቶች እንደመደበኛ በጎፈቃደኛ አይቆጠሩም እና በዚህ ወቅት የ MCPS ሠራተኞች ይቆጣጠሯቸዋል። |
| **ጥ14፡- ወላጆች/ሞግዚቶች ተማሪዎች በሚለቀቁበት ወቅት ወይም በእረፍት ሠዓት የሚረዱ ከሆነ ስልጠና መውሰድ አለባቸው?** | **መ** 14፡- አዎ። በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ት/ቤት በሚያካሄዳቸው እንቅስቃሴዎች ከተማሪዎች ጋር የሚሠሩ ወላጆች/ሞግዚቶች በትምህርት ቤት ውስጥ በጎፈቃደኝነት ከመጀመራቸው በፊት በድረ-ገጽ ስልጠና ማሟላት አለባቸው። |
| **ጥ15፡- ት/ቤትን የሚረዱ የ MCPS በጎ ፈቃደኛ - ተማሪዎች በድረ-ገጽ ላይ የበጎፈቃደኛ ስልጠና መሙላት ይኖርባቸዋል?** | **መ** 15፡- አይደለም በትምህርት ቤት እየረዱ ያሉ የ MCPS በጎፈቃደኛ-ተማሪዎች ሁልጊዜም በ MCPS ሠራተኛ አማካይነት ቁጥጥር ይደረጋል። |
| **ጥ16፡- ተማሪ መምህራን እና interns በድረ-ገጽ የበጎፈቃደኛ ስልጠና መሙላት ይኖርባቸዋል?** | **መ** 16፡- አዎ። ተማሪ አስተማሪዎች እና interns "Child Abuse and Neglect" የግዴታ/mandatory ስልጠና በድረ-ገጽ [እዚህ](link) እንዲሞሉ ይጠበቅባቸዋል። |

## የጣት አሻራና የኃላ ታሪክ ማጣራት/ Background Check አስፈላጊነት/ግዴታዎች፡-

| **ጥያቄ** | **መልስ** |
|---|---|

| | |
|---|---|
| **ጥ17፦ ለበጎፈቃደኞች የበፊት ታሪካቸውን ማረጋገጫ መስፈርቶች/background check requirements ምንድናቸው?** | **መ 17፦** በሚከተሉት ምድቦች ውስጥ ያሉት በጎ ፈቃደኞች የጣት አሻራ እና የበፊት ዳራ ማጣራት ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል፦<br>• በጎ-ፈቃደኛ አሰልጣኞች፣<br>• የ 6ኛ ክፍል ከቤት ውጭ የአካባቢ ትምህርት ፕሮግራሞች (Environmental Education Programs) ታዳሚዎች (ቻፐሮኖች)፣<br>• ከአከባቢ ውጭ (ከሮክቪል አካባቢ 50 ማይል ወይም ከዚያ በላይ) እና/ወይም የሌሊት የመስክ ጉዞዎች ላይ የሚሳተፉ በጎ ፈቃደኞች፣ እና<br>• ለረዥም ቀን ጉዞ የበጎ ፈቃደኞች የትምህርት ቤት ድጋፍ እና ማሻሻያ ጽ/ቤት ማጽደቅ የሚያስፈልገዉ። (ለምሳሌ፦ የጉዞ መነሻ ሠዓት በ MCPS ሥራ የሚጀመርበት ሠዓት እና/ወይም የመመለሻው ሠዓት ከ7:00 p.m በኋላ ከሆነ)<br><br>[ማስታወሻ- በአንድ ቀን ከ 100 ማይል በታች የሚጓዙ የአትሌቲክስ/የስነጥበብ ጉዞዎች ቻፔሮን/በጎ ፈቃደኞች የጣት አሻራ ወይም የበፊት ታሪክ (ዳራ) ማጣራት አይጠበቅባቸውም።]<br><br>በስራ ላይ የሚገኙ የፌደራል፣ የስቴት፣ እና የአካባቢ ሕግ አስከባሪዎች በሥራ አቀጣጠር ምክንያት ያለፈ የወንጀል ማጣሪያ ያሚሉ እናም ከMCPS የበፊት ጥናት/ማረጋገጫ አይመለከታቸውም። ሆኖም የተቀጠሩበትን ኤጀንሲ የሥራ ቅጥር መታወቂያ ቁጥራቸውን ጭምር ለማረጋገጥ በ Backgroundscreening@mcpsmd.org የጣት አሻራ ጽሕፈት ቤት ማነጋገር ይጠበቅባቸዋል። ሌሎች ለሥራቸው (White House, a government agency, etc.) የጣት አሻራ ያላቸው በሙሉ፣ MCPS (ያለፈውን እና የወደፊት የወንጀል ድርጊቶችን) ሪፖርቶች ከኃላፊዎቹ ለመውሰድ እንዲችል በ MCPS ወይም American Identity Solutions (AIS) አማካይነት የጣት አሻራ መስጠት አለባቸው። |
| **ጥ18፦ በጎፈቃደኞች ስለበፊት-ስነምግባር ማጣሪያ ለማግኘት መሄድ ያለባቸው የት ነው እና ማጣሪያውን ለማግኘት ምን ያክል ጊዜ ይወስዳል?** | **መ 18፦** የጣት አሻራ እና የበፊት ታሪክ (ዳራ) ማጣራት መረጃ እዚህ ሊገኝ ይችላል። ቀጠሮ ያስፈልጋል፦<br>**ጊዜያዊ ቦታ፦ Emory Grove Center (EGC)**<br>18100 Washington Grove Lane, Gaithersburg, Maryland 20877<br>202-641-4366 or 202-641-4825 or Backgroundscreening@mcpsmd.org<br>የዳራ ማጣራት ሂደት ለማጠናቀቅ በግምት አራት ሳምንታት ይወስዳል። |
| **ጥ 19፦ የበጎ ፈቃደኞችን የበፊት ታሪክ ማጣራት ለማጠናቀቅ ማን ይከፍላል?** | **መ 19፦** የበጎ ፈቃደኛው የበፊት ታሪክ ማጣራት ወጪ ተጠያቂ ነው። ዋጋው 55.25 ዶላር (ጥሬ ገንዘብ) ወይም 56.45 ዶላር (ክሬዲት ካርድ) ነው።<br>እያንዳዱ ጉዳይ እየታየ፣ ወጪዎቹ የሚሸፈኑበትን መንገድ ት/ቤቶች ከበጎ-ፈቃደኞች ጋር ሊነጋገሩ ይችላሉ።<br><br>• ከቤት ውጭ ትምህርት የሌሊት ቻፔሮኖች ለበፊት ታሪክ ማጣራት ምንም ወጪ አይኖርባቸውም።<br>• በጎ-ፈቃደኛ አሰልጣኞች፣ በአትሌቲክ መምርያ በኩል እንደተዘጋጀው፣ የአለፈ ታሪክ ለማጣራት/background checks መክፈል ይቀጥላሉ። |
| **ጥ 20፦ የ MCPS ያለፈ ታሪክ ማጣራት ባለፈው አመት ከፈፀምኩ ሌላ ያለፈ ታሪክ ማጣራት ማድረግ አለብኝ ወይ?** | **ጥ 20፦** ወላጅ/አሳዳጊ/የማህበረሰብ አባል ከዚህ ቀደም በ 2019-2020 ወይም 2020-2021 የትምህርት ዓመት የ MCPS የበፊት ታሪክ የማጣራት ሂደቱን ካጠናቀቀ(ች)፣ በአሁኑ ጊዜ በ 2021-2022 የትምህርት ዓመት ሂደቱን እንደገና ማጠናቀቅ የለበትም።<br><br>በአዲሱ የፌደራል **Rap Back** መመሪያዎች (የእስር እና የክስ የኋልዮሽ ሪኮርድ ፕሮግራም) ምክንያት፣ ተፈላጊ መስፈርቶች እየተተገበሩ ሲሆን ይህ መረጃ በክለሳ ላይ ነው።<br><br>ለወቅታዊ መረጃ እባክዎ ይህንን በይነመረብ Backgroundscreening@mcpsmd.org ይመልከቱ፦ |

| | |
|---|---|
| **ጥ 21፡- የት/ቤት ወላጅ መምህር (ተማሪ) ህብረት (PTA/PTSA) ከትምህርት-በኋላ እንቅስቃሴ፣ የሰውነት ማጎልመሻ ፕሮግራም፣ ወይም ሌላ ፕሮግራም ስፖንሰር ቢያደርጉ፣ የ MCPS ኮንትራክተሮችን የሚመለከተው የበፊት-ስነምግባር ማጣራት እና የጣት አሻራ የማቅረብ መስፈርት እነዚህንም ይመለከታቸዋል?** | ***መ* 21፡-** በትምህርት ቤት ለሚደገፉ ዝግጅቶች ብቻ የጣት አሻራ እና የጀርባ ምርመራዎች ያስፈልጋሉ። <br>● ከትምህርት-ውጭ ፕሮግራሙ በMCPS ገንዘብ ከተሰጠው ወይም ስፖንሰርድ ከሆነ ወይም MCPS የኮንትራቱ አካል ከሆነ (ይህም ማለት፣ የርእሰ መምህሩ/ሯ ፊርማ ኮንትራቱ ላይ ካለ)፣ ስልጠና ያስፈልጋል እናም የትምህርት-ውጭ ፕሮግራሙ አቅራቢዎች ቀጥተኛ፣ ቁጥጥር የሌለው መዳረሻ ወደ MCPS ተማሪዎች በ MCPS አገልግሎት መስጫ መዳረሻ ካለው የአለፈ ታሪክ ማጣራት/background checks ይፈለጋል። <br>● ቾንትራቱ በት/ቤት ስፖንሰርድ ካልሆነ እና ብቸኛ ስፖንሰር PTA/PTSA ወይም ሌላ ድርጅት ከሆነ፣ ወይም Interagency Coordinating Board/የወኪል ድርጅቶች አስተባባሪ ቦርድ (ICB) ብቻ ከተደራጀ፣ MCPS የአለፈ ታሪክ ቁጥጥር ወይም ስልጠና አይጠይቅም። ቢሆንም፣ PTA/PTSA ወይም ICB ለስራ ተቋራጮቻቸው ተጨማሪ ግዴታዎች ሊኖሯቸው ይችላል። |
| **ጥ 22፡- በበጎ-ፈቃደኛነት ለማገልገል ዝንባሌና ፍላጎት ያላቸው ፈቃድ ማግኘታቸውንና አለማግኘታቸውን ማን ይነግራቸዋል?** | ***መ* 22፡-** በጎ ፈቃደኞች ሊሆኑ የሚችሉ ብቻ የስቴቱ የበፊት ዳራ ማጣራት ውጤት በፖስታ ማሳወቂያ ይደርሳቸዋል። ስለ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎች፣ የሕፃናት ወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎች እና የአመፅ ወንጀሎች እንዲሁም የአደገኛ ዕፆችን ስርጭት ወይም ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮችን የሚያካትቱ ማናቸውንም ወንጀሎች በተመለከተ MCPS እንደየጉዳዩ አንድ በአንድ ትንተና ያካሂዳል እና ከበጎፈቃደኛ ጋር ወዲያውኑ ክትትል ያደርጋል። ስለ በጎፈቃደኛ የወንጀል ዳራ ማጣራት በተመለከተ ትምህርት ቤት ለሚገኙ ሰራተኞች MCPS ማንኛውንም ዝርዝር ይፋ አያደርግም። |
| **ጥ 23፡- ስለ በጎ ፈቃደኞች ሥልጠና እና የበፊት ታሪካቸውን ማጣራት ጥያቄዎች ካሉኝ ማንን ማነጋገር አለብኝ?** | ***መ* 23፡-** ስለ በጎ ፈቃደኝነት መስፈርቶች ማናቸውም ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉዎት እባክዎን ትምህርት ቤትዎን ያነጋግሩ። <br><br>በተጨማሪም፣ በትምህርት ቤት ደረጃ ያልተነሱ ስጋቶች፡- <br>● ***የበጎ ፈቃደኞች* ስልጠና፡-** የተማሪ አመራር እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች 240-740-3977 <br>● ***የኋላ ታሪክ* ማጣራት፡-** የጣት አሻራ ጽ/ቤት ያነጋግሩ 202-641-4366 or 202-641-4825 Backgroundscreening@mcpsmd.org |
| **ጥ 24፡- በ MCPS ጣቢያዎች ላይ የሚሠሩ የሞንትጎመሪ ኮሌጅ ሠራተኞችን እነዚህ መስፈርቶች እንዴት ይመለከታቸዋል?** | ***መ* 24፡-** በሞንትጎመሪ ኮሌጅ የጣምራ ምዝገባ ፕሮግራም ሠራተኞች በሚቀጠሩበት ጊዜ የጣት አሻራ ጨምሮ የወንጀል ድርጊት ማጣራት ይደረግባቸዋል። ትምህርት ቤት ባሉበት ወቅት ከሞንትጎመሪ ኮሌጅ የተሰጣቸውን የመታወቂያ ባጅ በሚታይበት ሁኔታ ማድረግ አለባቸው። |
| **ጥ 25፡- ለሞንትጎመሪ ካውንቲ -አስተዳደር (MCG) እነዚህ መስፈርቶች እንዴት ሊተገበሩ ይችላሉ?** | ***መ* 25፡-** እንደ ነርሶች እና የጤና ክፍል ቴክኒሺያኖች ያሉ የ MCG ሠራተኞች በሚቀጠሩበት ጊዜ አሻራን ጨምሮ የበፊት የወንጀል ድርጊት ማጣራት ይደረግባቸዋል። ትምህርት ቤት በሚሆኑበት ወቅት ከ MCG-የተሰጣቸውን የመታወቂያ ባጅ በሚታይ ሁኔታ ማድረግ አለባቸው። MCPS የወንጀል ማጣራት ሂደት ላጠናቀቁ ከትምህርት ፕሮግራሞች ጋር ለሚገናኙ የካውንቲ ሠራተኞች በሙሉ የመታወቂያ ካርድ ይሰጣቸዋል። |
| ***** አዲስ የኮቪድ-19 ማረጋገጫ መስፈርቶች ከጥቅምት 1 ቀን 2021 ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናሉ***** | |
| **ጥ 26፡- ለአዲስ በጎ ፈቃደኞች የ COVID-19 ፕሮቶኮሎች ምንድናቸው?** | **አዲስ *በጎ ፈቃደኞች*** - ሁለቱን ሞጁሎች ማጠናቀቅ አለባቸው፡- <br>● በኦንላይን myMCPS Classroom/Canvas አካውንታቸው ስለ ሕፃናት በደልና ቸልተኝነት ግንዛቤ ሥልጠና <br>● (ብስኬታማነት ሲያጠናቅቁ የተገኘው ውጤት 100% ያሳያል) <br>● የኮቪድ-19 የክትባት ማረጋገጫ - አዲስ! (ሴፕቴምበር 20/2021 ይገኛል) (በስኬታማነት ካጠናቀቁ የተገኘው ውጤት 83.3% ያሳያል) <br>**የወቅቱ *በጎ ፈቃደኞች*** - አዲሱን የ ኮቪድ -19 የክትባት ማረጋገጫ ሞጁል ያጠናቅቁ (ሴፕቴምበር 20/2021 ይገኛል) <br>(በስኬታማነት ካጠናቀቁ የተገኘው ውጤት 83.3% ያሳያል) |

| | |
|---|---|
| **ጥ 27፦ ለአሁኑ በጎ ፈቃደኞች የ COVID-19 ፕሮቶኮሎች ምንድናቸው?** | **የወቅቱ በጎ ፈቃደኞች** - አዲሱን የ ኮቪድ -19 የክትባት ማረጋገጫ ሞጁል ያጠናቅቁ (ሴፕቴምበር 20/2021 ይገኛል)<br>(ለስኬት ማጠናቀቂያ የተገኘው ውጤት 83.3% ያሳያል) |
| **ጥ 28፦ በጎ ፈቃደኞች የኮቪድ -19 ማረጋገጫ ሞጁሎችን እንዴት ያገኛሉ?** | ሞጁሎች እና የተጠቃሚ መመሪያ በሁለቱም ድረ-ገጾች ላይ ሊገኙ ይችላሉ https://www.montgomeryschoolsmd.org/childabuseandneglect/ እና https://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/student-leadership/volunteer.aspx<br><br>ሁለቱንም ሞጁሎች ያጠናቀቁ በጎ ፈቃደኞች በፀደቀው የበጎ ፈቃደኝነት ዝርዝር ውስጥ እንደሚቆዩ እና በት/ቤቱ ተለይተው በሚታወቁ ፍላጎቶች ላይ በመመስረት ፈቃደኛ ሊሆኑ ይችላሉ።<br><br>ሁለቱንም ሞጁሎች ያልጨረሱ በጎ ፈቃደኞች ከእንግዲህ በዝርዝሩ ውስጥ አይገቡም።<br><br>የሕፃናትን በደል እና ቸልተኝነት ሥልጠና (2019-2020፣ 2020-2021፣ እና 2021-22) ኦንላይን የወሰደ(ች) ማንኛውም በጎ ፈቃደኛ ኮቪድ-19 የክትባት ማረጋገጫ ሞጁል ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ በጎ ፈቃደኛ ዝርዝር ውስጥ ይመለሳል። |